የሰ/መ/ቁ. 35440

ግንቦት 19 ቀን 20000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት - ምንተስኖት ተፈሪ /ነገረ ፈጅ/ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ብርሃኔ አሊማ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ እሱም ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ባቀረበው ክስ የአዋጁን አንቀጽ 29 በሚቃረን መልኩ በሠራተኛ ቅነሳ ሰበብ የሥራ ውሌ ተቋርጦብኛል እና ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከስራው የተሰናበተው ድርጅቱ በመክሰሩ የተነሣ ሠራተኞችን መቀነስ አስፈላጊ /ግዴታም/ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ ተጠሪ ድርጅቱን ለማዳን /እንዳይዘጋ ለማድረግ/ ሲባል በተደረገው የመዋቅር ለውጥ የሚመጥነው የስራ መደብ አልተገኘም፡፡ ቅነሳው የተካሄደው ሕጉን ተከትሎ የድርጅቱ ሠራተኛ ማኅበርም በተሳተፈበት ሁኔታ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዱም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ቅነሳው ሕጉን የተከተለ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማለቱ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የቦርዱን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ ወደ ስራው እንዲመለስ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የጠ/ፍ/ቤቱ የቦርዱን ውሣኔ የሻረበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ተጠሪን ከስራ ውጪ ያደረገው የሠራተኛ ቅነሳ ሕጉን ተከትሎ የተደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ከተደረገው ክርክር እና ቦርዱ ከሰጠው ውሣኔ እንዳየነው አመልካች ድርጅት ከ75% በላይ ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡ ድርጅቱ በመክሰሩም የነበረው አማራጭ መፍረስ ቢሆንም፣ አፍርሶ ከመሄድ ይልቅ ሌላ አማራጭ ፈልጎ ሕልውናውን ማቆየት ይሻላል በሚል ሠፊ ጥረትና ጥናት ከተካሄደ በኋላ አዲስ የስራ መዋቅር በማዘጋጀት ሠራተኞቹ ባላቸው የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ መሠረት ምደባ መደረጉንም ቦርዱ አረጋግጦአል፡፡ በመጨረሻም የድርጅቱ የሠራተኛ ማኅበር በተሳተፈበት የሠራተኛ ቅነሳ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በአዲሱ የሥራ መዋቅር ለመመደብ የትምህርት ዝግጅቱ የሚፈቅድለት ሆኖ ባለመገኘቱ እንዲቀነስ መደረጉን በቦርዱ ውሣኔ ላይ ቁልጭ ብሎ መቀመጡን በበኩላችንም ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ እንግዲህ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠውን ሁኔታ በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ካለው የአዋጁ አንቀጽ 29/3/ ጋርም የሚስማማ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያመለክተው በአዋጁ አንቀጽ 28/1/ መሠረት የሠራተኞች ቅነሳ በሚደረግበት ጊዜ አሠሪው ከሠራተኞች ማኅበር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር የስራ ችሎታ ያላቸውንና ከፍተኛ የምርት ውጤት ያሳዩ ሠራተኞችን በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባው ነው፡፡